በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ




# ከጁላይ 11-20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና

# ከጁላይ 21-31 እና ከኦገስት 1-10/2026 የሚኖረው

# የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2026

አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ


ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ቦሌ 33.2፣ ባህር ዳር 52፣ 21.8፣ 23.3፣ ኮምቦልቻ 35.8፣ ጎሬ 38.5፣ ጅማ 96.3፣ 38.6፣ መተሃራ 20.5፣ ነቀምት 21፣ 50.7፣ ሮቤ 30.4፣ አይራ 36፣ አለምከተማ 26.5፣ አማን 21.7፣ አምባማሪያም 50.2፣ 42.6፣ አምደወርቅ 24.4፣ አንገርጉትን 23.6፣ አርጆ 28.4፣ 20.6፣ አሶሳ 39.5፣ አዋሽ አርባ 25፣ አይከል 28.3፣ 25.3፣ በደሌ 20.3፣ ቦሬ 36.6፣ ቡሂ 25.3፣ ቡለን 20፣ ቡሬ 58.8፣ 76.2፣ ጭራ 25.7፣ 70፣ 26.8፣ ደባርቅ 31፣ ደብርብርሃን 32.7፣ ደብርታቦር 20.1፣ 34.4፣ ደምቢዶሎ 25.2፣ 36.3፣ ፊቼ 22.4፣ ፉኙዶ 36.6፣ 48፣ ጋቲራ 21.8፣ ገለምሶ 22፣ ጊዳአያና 25.8፣ ጊምቢ 22.3፣ 25.7፣ ጉንዶመስቀል 31.7፣ ሆሳዕና 41.1፣ እምድብር 22.6፣ ጅንካ 21.9፣ ካቺሴ 44.4፣ 27.7፣ ሊሙገነት 62.7፣ 22፣ ማጂቴ 29.5፣ ማንኩሽ 26፣ 22.2፣ መሃልሜዳ 47.6፣ መተማ 29.2፣ ሞጣ 24.1፣ ነጆ 22.2፣ 39.7፣ ሳሁላ 20፣ ሻሁራ 21፣ 22.1፣ ሻምቡ 40.8፣ ሾላገበያ 50.7፣ ተርጫ 25.6፣ ወረኢሉ 47፣ የትኖራ 26.4፣ አባይ ሸለቆ 20.3፣ ኦቦሞሪንጋ 36.3፣ አዳሚቱሉ 29.3፣ አዲስዘመን 20፣ አጋሮ 22.5፣ አቃቂ 21፣ አንጋጫ 23፣ አንኮበር 27.1፣ አሺ 22.4፣ 26፣ 32.4፣ 22.8፣ አሸሬ 22.8፣ አሳሳ 25፣ ቡልቂ 26.4፣ 36.6፣ 26፣ 36.1፣ ጨፌዶንሳ 31.2፣ ጨለንቆ 26.8፣ ደበረሲና 23.9፣ ደነባ 27.3፣ ጋሳይ 33.2፣ 29.2፣ ጋሸና 26.7፣ ጊሸራቤል 44፣ ጎብየሬ 20.8፣ 35.6፣ ጉጉፍቱ 38.2. 49.6፣ ሃይቅ 20.8፣ ሃሮ 20.2፣ ሆሮዶዮ 30፣ ቅዳሜ ገበያ 26.7፣ 20.4፣ 36.6፣ 27.8፣ 26.7፣ 20.8፣ ኮሶበር 30.5፣ 36.4፣ ላሎቂሎ 22.4፣ 26.5፣ 29.1. ማርዬ 20.4፣ ማያንሳ 39.4፣ መቂ 24፣ ኦሞናዳ 28፣ 31.2፣ 28.8፣ ኦንጋ 21.6፣ 24.8፣ 30፣ ሰዲቃ 27.2፣ 21.9፣ ሸብለበረንታ 25.5፣ ሼንዲ 21.5፣ ተርኮዲ 20.5፣ 26.8፣ ፅጌረዳ 20.7፣ መንደር13 24.2፣ 34.2፣ 32.4፣ 30.4፣ መንደር11 20፣ 46.5፣ 22፣ ገምቤ 25.4፣ እንዲሁም ሮቤሃይስኩል 26.5 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል። በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ44 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብና የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.8-96.3 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ45 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል በጅማ፣ ቡሬ፣ ጭራ፣ ሊሙገነት፣ ባህርዳር፣ ነቀምት፣ ሾላ ገበያ፣ አምባ ማሪያም ጉጉፍቱ፣ ፉኙዶ፣ መሃልሜዳ፣ ወረኢሌ፣ መንደር11 ይገኙበታል፡፡

Ethiopian Meteorology Institute


ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ31-190 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ አዲስ አበባ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ጁላይ 11 እስከ 20 /2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ጁላይ 11 እስከ 20 /2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ጁላይ 11 እስከ 20 /2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር


## 1.2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በተለይም በሰሜን፤ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት ነበራቸው። ይህም ሁኔታ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት ጥሩ አስተዋጾ የነበረው ሲሆን፤ እንዲሁም የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እድገት የጎላ አስተዋፅዖ ነበረዉ። በተጨማሪም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ የነበረው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተፈጥሮንም ሆነ የሰው ሰራሽ የውሃ ምንጮችን በማጎልበት ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በአንጻሩ በተወሰኑ የሰሜንና የሰሜን ምስራቅ የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከዝናብ መቆራረጥ ጋር ተያይዞ የአፈር ውስጥ እርጥበት እጥረት የተስተዋለ ሲሆን ይህም ሁኔታ በተዘሩ ሰብሎች እድገት ላይ መጠነኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት ጋር ተያይዞ የደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው (ካርታ 4)።


## 1.3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የጁላይ ሁለተኛ አሥር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ በላይኛውና መካከለኛ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛውና መካከለኛ ዋቢ ሸበሌ እንዲሁም በላኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው። በተጨማሪም ተከዜ፣ አባይ፣ በላይኛው አዋሽ፣ በመካከለኛው ኦሞ ጊቤና ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ የገጸምደረ የውሃ ፍሰት የነበረ ሲሆን በተጨማሪም በመካከለኛ አዋሽ፣ በአፋር ደናክል፣ በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ እንዲሁም በላይኛው ተከዜ፣ በአይሻ እና በላይኛው ጥቂት የኦጋዴን ተፋሰሶች ከመጠነኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ነበራቸው። ይህ ሁኔታ ለገጸ ምድር፣ ለከርሰ ምድር፣ ለመስኖ፣ ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን

ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ አስተዋፅዎ እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

Ethiopian Meteorology Institute

## 2. እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በጁላይ ሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካር 6)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ ሰሜን፣ መካከለኛው፣ ሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ይኖራቸዋል (ካርታ 6) በመሆኑም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና ሰሜ የሀገራችን አከባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ ሰሜ ምስራቅ፣ ምስራቅና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 )፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 21-31/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

### 2.1 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6) ፡፡


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ጥቂት የምስራቅ ቦረና ዞን | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ | ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ1-30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ1-30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የፋንቲ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ፣ ፋፈን እና ዳዋ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.2 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ


በጁላይ የሁለተኛው አስር ቀናት ከሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ፤ በተለይም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊ ዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኚዶ አከባበዎች ላይ ከ24 እስከ 40 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 21-31/2026, የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ የኦገስት መጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እሰከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ (ከ1-29 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

Ethiopian Meteorology Institute

## 2.4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የጁላይ ወር ሶስተኛ አስራ አንድ ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በሰሜን የሀገራችን አከባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በመካከለኛው፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀምና የሚጠበቁ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2) ፡፡

## 2.5 እ.አ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን የሚደረስ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የሚኖሩ መልካም ዕድሎችን በአግባቡ ለመጠቀምና ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3) ፡

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ እንዲሁም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች | | | |
|---|---|---|---|
| **ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የተሰጠ ምክረ ሃሳብ** |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ የደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ አዊ ፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ፣ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ፣ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች | ➢የአፈር ዉስጥ እርጥበት መሻሻል<br>➢ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገትና የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት<br>➢ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ለቋሚ ተክሎች እድገት | ➢የእርጥበት መብዛት፣ የማሳዎች መጨቀየት እና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>➢ውሃገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ<br>➢ በልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች የደረሱ የበልግ ሰብሎች በእርጥበት መጎዳት<br>➢የአረም መከሰት<br>➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት | ➢ የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር ሰብሎችን ዘር መዝራት<br>➢ ተዳፋታማ ማሳዎች ላይ የተዘሩ የማፋሰሻና የማንጣፈፊያ ቦዮችን ማስተካከል<br>➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ የአፈር መሸርሸር መከላከል ስራዎችን በስፋት መስራት<br>➢ የመሬት መንሸራተት ተጋላጭነትን መቀነስ<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>➢ አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር<br>➢ በልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በየጣልቃው የሚኖሩ ደረቅ ቀናቶችን በመጠቀም መሰብሰብ |

| ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ጥቂት የምስራቅ ቦረና ዞን፣ ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ፋንቲ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ሲቲ፣ ፋፈን እና ዳዋ ዞኖች | ➢ ለመኸር ሰብሎችን ዘር ለመዝራት ምቹነት<br>➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል<br>➢ ለከተማ አካባቢ ግብርና ስራ | ➢ የዝናብ መቆራረጥና ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>➢ የትነት መጠን መጨመር፤<br>➢ የሰብል በሽታ መከሰት፤<br>➢ የአፈርና ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን<br>➢ በልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች የደረሱ የበልግ ሰብሎች በእርጥበት መጎዳት | ➢ የሚገኘዉን እርጥበት በቂ መሆኑን በማረጋገጥ የመኸር ሰብሎችን ጊዜውን ጠብቆ መዝራት<br>➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>➢ የአፈር ትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን<br>➢ የአፈር እቀባ ስራ ማከናወን<br>➢ የእንስሳት ግጦሽ ሣር በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤<br>➢ የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በየጣልቃው የሚኖሩ ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም መሰብሰብ |

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከባድ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| • በይኛውና መካከለኛ አባይ፣ አዋሽ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛና ታችኛው ተከዜ በላኛዉና መካከለኛው በላኛዉ ስምጥ ሸለቆ፣አዋሽና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ መጠን መሻሻል<br>• የመጠጥ ውኃ አቅርቦት መሻሻል<br>• የከርሰ ምድር የውኃ መጠን መሻሻል | • ቅፅበታዊ ጎረፍ መከሰት<br>• የደለል ስጋት መጨመር<br>• የውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች በቆሻሻ መዘጋት | • የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• የመጠጥ ውሃን አክሞ መጠቀም<br>• የፍሳሽ መውረጃ ቦዮችን ማፅዳት<br>• የጎርፈ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• ወራጅ ውሃን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር<br>• ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| • መረብ ጋሽ፣ ላይኛውና መካከለኛ ተከዜ፣ መካከለኛውና ታችኛው አዋሽ፣ ላይኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል<br>• የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ | • ዝቅተኛ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች መጠነኛ የውሃ እጥረት | • የሚገኘውን የዝናበ ውሃ አክሞ መጠቀም<br>• ወራጅ የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውሃ የማሰባበሰብ ማጠራቀም<br>• የአየር ሁኔታ መረጃን በቅርበት መከላከል |
| **በደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| ኦጋዴን፣ አይሻ፣ታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር፣ | የገጸ ምድር የውሃ የትነት መጨር | • የሚገኘውን ውሃ በቁጠባና ውጤታማ መጠቀም |